የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ — ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 9
ADDIS ABABA – 5th December, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ........................................................ ገጽ ፪፻፹፰

## CONTENTS

Proclamation No. 52/1996

Ethiopian Privatization Agency Establishment (Amendment) Proclamation ...................... Page 288

### አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፱

### የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲን ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩· ከአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል ፤

"፬· የኤጀንሲውን መዋቅርና የኤጀንሲው ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች በመከተል የተዘጋጀ መመሪያ ያጸድቃል ፤"

፪· የአንቀጽ ፰ የቀድሞዎቹ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፤ (፭) እና (፮) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፭) ፤ (፮) እና (፯) ሆነዋል።

፫· በአንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ሐ) ውስጥ "በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ቦርዱ ባጸደቀው መመሪያ መሠረት" በሚለው ተተክቷል ።

### PROCLAMATION No. 52/1996

### A PROCLAMATION TO AMEND THE ETHIOPIAN PRIVATIZATION AGENCY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Ethiopian Privatization Agency Establishment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Privatization Agency Establishment (Amendment) Proclamation No. 52/1996."

2. *Amendment*

The Ethiopian Privatization Agency Establishment Proclamation No. 87/1994 is amended as follows:

1) The following new sub-Article (4) is added after sub-Article (3) of Article 8:

"4) approve the organizational structure of the Agency and directives on its staff regulation prepared in line with the basic principles of federal civil service laws;"

2) The former sub-Articles (4),(5) and (6) of Article 8 are renumbered as sub-Articles (5), (6) and (7), respectively.

3) The phrase "in accordance with the public service laws" appearing in sub-Article (3) (c) of Article 10 is deleted and replaced by the phrase "in accordance with directives approved by the Board."

፫. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of the 5th day of December, 1996.

Done at Addis Ababa, this 5th day of December, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE